**መግቢያ**

የተለያዩ ዓለም አቀፍና ብሔራዊ ህግጋት ምግብ የማግኘት መብትን እንደ አንድ የሰብአዊ መብት እውቅና ሰጥተውታል። ከእነዚህም ውስጥ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ኮንቬንሽን አንዱ ሲሆን፤ በዚሁ ኮንቬንሽን አንቀፅ 11 ላይ በቂ ምግብ ማግኘት የሰብአዊ መብት መሆኑ በግልፅ ተረጋግጧል። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኮንቬንሽኑን ተፈፃሚነት ለመከታተል የተቋቋመው የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ኮሚቴ በሰጠው ትንታኔ፣

**በቂ ምግብ የማግኘት መብት**

◊ ተደራሽነት ያለው እና የተመጣጠነ ምግብ፣
◊ በጥራትና በብዛት በመገኘት የግለሰቦችን የተመጣጠነ ምግብ የመመገብ ፍላጎት የሚያረካ፣
◊ ጎጂነት ካላቸው ንጥረ ነገሮች የፀዳ፣
◊ በአንድ ማህበረሰብ ባህል መሠረት ተቀባይነት ያለው ምግብ የሚሉትን መስፈርቶች እንደሚያጠቃልል ገልጿል።

**1. ተደራሽነት /Accessibility/**

ተደራሽነት የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ሁለት ነገሮችን ያካትታል። እነዚህም ኢኮኖሚያዊና አካላዊ /Economic and Physical/ ተደራሽነት ናቸው።

ሀ. **ኢኮኖሚያዊ ተደራሽነት /Economic Accessibility/** የሚባለው አንድ ግለሰብ ወይም ቤተሰብ ለሕልውናው ወሳኝ የሆነውን የተመጣጠነ ምግብ ገዝቶ ለመጠቀም የሚያስችለውን የገንዘብ አቅም ይመለከታል።

በገበያ ውስጥ ያሉት ተመጣጣኝ ምግቦች ዋጋ ከተጠቃሚው ህብረተሰብ የመግዛት አቅም በላይ መሆን የለበትም፣ አንድ ሰው በአቅም ማጣት ሳቢያ ምግብ የሚያገኘው ሌሎች መሠረታዊና ሰብአዊ የሆኑ መብቶችን በመተው ወይም በመጉዳት ሊሆን አይገባም። በዚህ ረገድ በተለይም ለዝቅተኛ የኅብረተሰብ ክፍሎች መሬት ወይም ሥራ ለሌላቸው ድሆች የተለየ ትኩረት መስጠትን ይመለከታል።

ለ. **አካላዊ ተደራሽነት /Physical Accessibility/** ይህ የሚያመለክተው ለሕልውና ተፈላጊ የሆነውን ምግብ ለማግኘት ተጠቃሚውና ምግቡ ያለበትን ስፍራ ርቀት ወይም ምግቡን ለማግኘት መቻልን ነው። አካል ጉዳተኞች፣ የአእምሮ ህሙማን፣ ህፃናትና ወጣቶች፣ አረጋውያን፣ የአልጋ ቁራኛ የሆኑ ህሙማን፣ የተፈጥሮ አደጋ ተጠቂዎች፣ ለአደጋ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች በአጠቃላይ ሁሉም ሰው ተመጣጣኝ የሆነ ምግብ በአቅራቢያው ሊያገኝ ይገባዋል።

**2. የተመጣጠነ የምግብ ውሁድ /Dietry Need/**፤ ማለት የሚቀርበው ምግብ የተመጋቢውን አካላዊና አዕምሮአዊ እድገት የሚጠብቅ፣ ለማደግ የሚያግዝ እንዲሁም የተመጋቢውን ጾታና ሥራ መሠረት በማድረግ ተመጋቢው በሕይወት ዘመኑ ለሚያከናውናቸው ሥራዎች ሁሉ ብቁ የሚያደርገው ምግብ ማለት ነው። ስለዚህ መንግስት በአገሪቱ ያለውን የአመጋገብ ሥርዓት በማጥናት ዜጎች የተጠቀሰውን ዓይነት ምግብ ማግኘት እንዲችሉ ያሉትን ጠቃሚ አመጋገቦች በመጠበቅ፣ ጠቃሚነት የሌላቸውን ደግሞ በሌ



ሁሉም ሰው በመጠንና በጥራት በቂ ምግብ
የማግኘት መብት አለው!

ሎች ምግቦች በመቀየር የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች እንዲኖሩ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለባት። ቀላል ምሳሌ ለመጥቀስ የእናት ጡት ወተት ለሕፃኑ አካላዊና አእምሮአዊ ጥንካሬ የሚሰጠው ጠቀሜታ ወሳኝ በመሆኑ፣ ሕፃኑ በበቂ ሁናቴ የእናቱን ጡት ወተት መመገብ አለበት።

**3. ጎጂነት ካላቸው ንጥረ ነገሮች የፀዳ መሆን /Free from adverse substances/**

በመንግስትም ይሁን በግለሰቦች አማካኝነት የሚቀርቡ ምግቦች ያልተበከሉ፣ ያልተመረዙ፣ ያልተበረዙና በንጽህና የተያዙ መሆን አለባቸው። ከዚህ በተጨማሪ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ የሚከሰቱ ምግብን የሚመርዙ ነገሮች እንዳይከሰቱ ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። ለምሳሌ ወተት ውስጥ ውሃ መጨመር፣ በምግብ ቅቤ ውስጥ ሙዝ መደባለቅ፣ በምግብ በርበሬ ውስጥ ሸክላ አፈር መቀላቀል፣ የቆየና በንጽህና ያልተያዘ እንጀራ ወይም ወጥ ለተመጋቢ ማቅረብ ህገወጥ ድርጊቶች ናቸው።

**4. ባህላዊ ተቀባይነት /Culturally acceptable/**

አንድ ምግብ ለጤና ተስማሚና ንፁህ መሆኑ ብቻ ምግብ ከማግኘት ሰብአዊ መብት አንፃር በቂ አይደለም። የሚቀርበው ምግብ ማህበረሰቡ ከሚከተለው ባህል ወይም እሴት ጋር በተቻለ መጠን የተዛመደ መሆን ይጠበቅበታል። የፈረስ ወይም የአህያ ሥጋ ለምግብነት በማይታሰብበት ማህበረሰብ ውስጥ የእነዚህን እንስሳት ሥጋ ለመሸጥ የሚፈልግ ነጋዴ ሥጋው የአህያ ወይም የፈረስ ስለመሆኑ በግልፅ ለተጠቃሚው በቅድሚያ ማሳወቅ ይጠበቅበታል። መንግስትም ይህን የመቆጣጠር ሃላፊነት አለበት።

በመሆኑም አንድ በተወሰነ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኝ የምግብ አይነት ለአእምሮና አካላዊ እድገት በእርግጥም ተፈላጊ የሆኑትን ንጥረ ነገሮች መያዝ ያለመያዙ በቅድሚያ ሊመረመር ይገባዋል። እንዲሁም ለተመጋቢው ህብረተሰብ፣ በምግቡ ንጥረ ነገር ላይ ስለተደረሰበት የምርመራ ውጤት ማሳወቅን ይጠይቃል።

**5. በጥራትና በብዛት ተሟልቶ መገኘት /Availability both in quality and quantity/**

ምግብ ከማግኘት መብት ጋር የተያያዘው ሌላው መስፈርት ተጠቃሚው በሚፈልገው መጠንና ጥራት ምግብ ማግኘት መቻል ነው። «**ተሟልቶ መገኘት**» የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ተፈላጊውን ምግብ በቀጥታ በማምረት ወይም ተፈጥሮ የለገሰውን በመጠቀም፣ እራስን መመገብ መቻል ወይም የምግብ ምርት ሥርዓት ባለው ግብይት ውስጥ በአግባቡ መሰራጨቱን፣ መመረቱን እና ከቦታ ወደቦታ በተለይም ከማምረቻ ቦታ ወደሚፈለግበት ቦታ ማንቀሳቀስ መቻልን ያጠቃልላል። በአንድ አገር የተወሰነ ክልል ውስጥ የተትረፈረፈ ምርት ኖሮ ገዢ በማጣት ወይም በዝቅተኛ ዋጋ ምርቱ ለሽያጭ ሲቀርብ በዚያው አገር ሌላ ክልል ላይ የሚኖሩ ሰዎች ደግሞ የመግዛት አቅም እያላቸው ተፈላጊውን ምርት በበቂና በጥራት ላያገኙ ይችላሉ። ስለዚህ ከምርት ሂደት በተጨማሪ የምርቱ ውጤት ለተጠቃሚው እንዲዳረስ ተገቢው ጥረት ሊደረግ ይገባል።

**6. ምግብ የማግኘት መብትና የመንግሥት ግዴታ**

ምግብ የማግኘት መብትን ተግባራዊ በማድረጉ ረገድ የመንግሥት ግዴታዎች በአለም አቀፉ የኢኮኖሚ፣

ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ኮንቬንሽን አንቀፅ 2 ላይ በግልጽ ተመልክቷል:: በመንግሥት ላይ የተጣለው ዋናው ግዴታ፣ ዜጎች የተመጣጠነ፣ ንፅህናው የተጠበቀ፣ተቀባይነትና ተደራሽነት ያለው ምግብ አግኝተው ከረሃብ የሚድኑበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ኢኮኖሚያዊ አቅሙ በፈቀደው መጠን በየጊዜው የሚሻሻል እርምጃ መውሰድ እንዳለበት ያመለክታል:: በአጠቃላይ ምግብ የማግኘት መብት እንደሌሎቹ ሰብአዊ መብቶች ሁሉ በመንግሥት ላይ ሦስት አይነት ግዴታዎችን ይጥላል:: እነዚህም መብቱን <u>የማክበር፣ የመጠበቅ/የማስከበር እና የማሟላት</u> ግዴታዎች ናቸው:: ቀጥለን እነዚህን ግዴታዎች በዝርዝር እንመለከታለን፤

**ሀ. <u>የማክበር /Respect/ ግዴታ</u>**

ይህ ግዴታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ዜጎች ምግብ የማግኘት መብታቸውን በተሟላ መልኩ መጠቀም እንዳይችሉ ከሚያግዱ አድራጎቶች እንዲቆጠብ በመንግሥት ላይ የተጣለ ግዴታ ነው:: ግዴታውም በሚከተሉት ምሳሌ ዎች ይገለፃል፣

◊ መንግሥት ዜጎች ለሕልውናቸው ቀጣይነት እየተ ጠቀሙበት ያለውን ስፍራ ወይም የተፈጥሮ ሀብት ለማጥፋት የሚያስችል ሕግ ማውጣት ወይም አስተ ዳደራዊ እርምጃ መውሰድ አይችልም::

◊ መንግሥት የተወሰኑ ግለሰቦችን ወይም የህብረተሰብ ክፍሎች ለይቶ ምግብ የማግኘት መብታቸውን መከልከል አይችልም::

◊ መንግሥት የሚያወጣቸው ሕጎች፣ ፖሊሲዎችና መመሪ ያዎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ዜጎችን የተ ሟላ ምግብ ከማግኘት የሚያግዷቸው መሆን የለባቸውም::

**ለ. <u>የመጠበቅ /Protect/ ግዴታ</u>**

ይህ ግዴታ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ዜጐች የተሟላ ምግብ እንዳያገኙ ወይም በአግባቡ መጠቀም እንዳይችሉ ከሚያደርጉ ተግባራት እንዲቆጠቡ መንግሥት አስፈላጊውን ጥበቃ እንዲያደርግ የተጣለበት ነው:: በመጠኑና በጥራቱ ደ ረጃውን ያልጠበቀ ምግብ በግለሰቦች ወይም በድርጅቶች ለህብ ረተሰቡ ሲሸጥ መንግሥት በዝምታ ሊመለከት አይገባውም:: ለምሳሌ የኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን በሚያደርገው የጥራት ቁጥጥር ሊጠበቅ ይችላል::

**ሐ. <u>የማሟላት /Fulfill/ ግዴታ</u>**

ይህ ግዴታ በመንግስት ላይ የተጣለው የዜጐችን ምግብ የማግኘት መብት የማሟላት ግዴታ የሚመለከት ሲሆን ምቹ ሁኔታ መፍጠር እና ተፈላጊውን ምግብ ማቅረብ የሚሉትን ያጠቃልላል::

የምግብ ዋስትናን ጨምሮ ዜጎች ለሕልውናቸው ወሳኝ የሆነውን የተመጣጠነና ንፅህናውን የጠበቀ ምግብ በሚፈልጉት መጠን እና ጥራት ማግኘት እንዲችሉ መንግሥት ሁኔታዎችን የማመቻቸት ግዴታ አለበት:: የሕዝቡን ኢኮኖሚያዊ አቅም በተለያዩ መንገዶች በማጠናከር ዜጎች መሠረታዊ የምግብ ፍላጎታቸውን እንዲያሟሉ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ረገድ ከመንግስት ከሚጠበቁት ግዴታዎች ውስጥ አንዱ ነው:: እንዲሁም ከአቅም ወይም ከቁጥጥር በላይ በሆነ ምክንያት አንድ ግለሰብ ወይም የተወሰነ ማህበረሰብ ክፍል ያላቸውን አቅም ተጠቅመው ለሕልውናቸው ወሳኝ የሆነውን ምግብ ለማግኘት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ሲገኙ መንግሥት ለነዚህ ክፍሎች ምግብ የማቅረብ ግዴታ አለበት:: ይህ ግዴታ በተፈጥሮ ወይም በሌላ ምክንያት አደጋ ላይ ለወደቁ ዜጎችም ሊፈፀም የሚገባው ነው::

መንግሥት እነዚህ ከላይ የተመለከቱትን ግዴታዎች በአግባቡ መወጣቱ ወይም አለመወጣቱ የሚወሰነው የመንግሥትን አቅምና ፈቃደኛነት በማየት ነው:: መንግሥት ግዴታውን እንዳልተወጣ የሚቆጠረው በአቅሙ ሊያደርጋቸው የሚገባቸውን ተግባራት ለመፈፀም ፍቃደኛ ሳይሆን ሲቀር ብቻ ነው:: መንግሥት በእጁ ያለውን ሀብት ዜጎች እንዲጠቀሙበት ከማድረግ ጀምሮ የተሟላ ምግብ የማግኘት መብትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን መንደፍና ዓለም አቀፍ እርዳታና ትብብር መጠየቅ ይጠበቅበታል::

የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ግዴታ በዋንኛነት በመንግሥት ላይ የተጣለ ቢሆንም ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ማለትም ግለሰብ፣ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ሲቪል ማህበራትና በግል ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩትን ጨምሮ፣ ዜጎች ከላይ በተ ገለፀው አይነት ጤንነቱ፣ ይዘቱ፣ መጠኑና አቅርቦቱ የተ መጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ የማገዝ ኃላፊነት አለባቸው:: መንግሥትም ህብረተሰቡ እነዚህን ኃላፊነቶች በአግባቡ እንዲወጣ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት:: በተለይም በምግብ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ለመልካም ሥነ ምግባር መመሪያ ተገዢ በመሆን ለዜጎች ሕልውና አስፈላጊ የሆነውን ጥራቱና መጠኑ የተጠበቀ፣ ዋጋው ተ መጣጣኝና የተጠቃሚውን የመግዛት አቅም ያገናዘበ ምግብ የማቅረብ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል::

# ምግብ የማግኘት መብት

ስድስት ኪሎ፣ወደ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል
በሚወስደው መንገድ ፤
ያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤትን አለፍ ብሎ፣
አዲስ የተሰራው የቴሌኮሚዩኒኬሽን ህንፃ ፊት ለፊት

ፖ.ሣ.ቁ. 12484፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ 251-11-1243555፣ፋክስ 251-11-1243558
ኢ-ሜይል:apap@ethionet.et
ዌብ ሳይት(ድረ-ገፅ): **http:**\\www.apapeth.org